**የአርብ ኹጥባ**

**(1)**

## የገበያ ስርኣቶችና ደንቦች

ምስጋና ሁሉ በተከበረው መጽሐፉ እንዲህ ለአለው የአለማት ጌታ ይገባው

وَيْلٌ لِلْمُطَفِّفِينَ *الَّذِينَ إِذَااكْتَالُوا عَلَى النَّاس يَسْتَوْفُونَ *وَإِذَا كَالُوهُمْ أَوْ وَزَنُوهُمْ يُخْسِرُونَ *أَلَا يَظُنُّ أُولَئِكَ أَنَّهُمْ مَبْعُوثُونَ * لِيَوْمٍ عَظِيمٍ *يَوْمَ يَقُومُ النَّاسُ لِرَبِّ الْعَالَمِينَ}

አጋር ከሌለው ብቸኛ አንድ አላህ በስተቀር በእውነት የሚገዙት እምላክ እንደሌለ እመሰክራለሁ፡፡ ነብያችን ሴዲና ሙሐመድም የእሱ ባሪያና መልእክተኛ በመሆናቸውም እምሰክራለሁ፡፡ ጌታዬ ሆይ! በርሳቸው በቤተሰቦቻቸውና በባልደረቦቻቸው እንዲሁም እስከቂያማ እለት በመልካም ምግባር በተከተሏቸውም ሰዎች ሁሉ ላይ እዝነትህን አውርድ፡፡

**ከዚህ በመቀጠል ክቡራን ሆይ፡**

አላሁ (አዘ ወጀል) ለባሮቹ ጉዳያቸው እንዲሳካና ፍላጎታቸው እንዲሟላ መሸጥ መለወጥን ፈቅዶላቸዋል፡፡ እንዲህም ይላል፡

وَأَحَلَّ اللَّهُ الْبَيْعَ وَحَرَّمَ الرِّبَا

ትርጉሙም ‹መሸጥን አላህ ፈቅዷል አራጥንም እርም አድርጓል› ማለት ነው፡፡ ሰዎች ከጥንት ጀምሮ ጥቅም የሚለዋወጡበትና የሚያስፍልጋቸውን ነገር የሚሸምቱበት ገበያ ቀንና ቦታ ወስነው መገበያትን ልምድ አደርገዋል፡፡ በዚህ ዘርፍ የወረዱት የቅዱስ ቁርኣን አንቀፆች ይህ ዓይነቱ ተግባር የሰው ልጅ ገፅታና ጠባይ መሆኑን ለማረጋገጥ እንደዎረዱ የእምነቱ ሊቆች ይጠቁማሉ፡፡ ታላቁ አላህ (ሱ. ወ.) እንዲህ ይላል

وَمَا أَرْسَلْنَا قَبْلَكَ مِنَ الْمُرْسَلِينَ إِلَّا إِنَّهُمْ لَيَأْكُلُونَ الطَّعَامَ وَيَمْشُونَ فِي الْأَسْوَاقِ

‹ትርጉሙም ከአንተ በፊትም ምልእክተኞች እነሱ በርግጥም ምግብን የሚበሉ በገበያዎችም የሚሄዱ ሁነው በስተቀር አላክንም› ማለት ነው፡፡ ቁርኣን አጀጋሪዎች ስለ ነብዩ ( ሶ.ዐ.ወ.) ያወሩትን እንዲህ በማለት ገልጹዋል፡፡

وَقَالُوا مَالِ هَٰذَا الرَّسُولِ يَأْكُلُ الطَّعَامَ وَيَمْشِي فِي الْأَسْوَاقِ

ትርጉሙም ‹ለዚህም መልእክተኛ ምግብን የሚበላ በገበያዎችም የሚሄድ ሲሆን ምን (መልእክተኛነት) አለው› አሉ ማለት ነው ፡፡ቁርአን የዋሻው ባለቤቶች ታሪክና ሁኔታን እንዲህ በማለት አብራርቷል፡፡

فَابْعَثُوا أَحَدَكُم بِوَرِقِكُمْ هَٰذِهِ إِلَى الْمَدِينَةِ فَلْيَنظُرْ أَيُّهَا أَزْكَىٰ طَعَامًا فَلْيَأْتِكُم بِرِزْقٍ مِّنْهُ

ትርጉሙም ‹ከዚህችም ብራችሁ ጋር አንዳችሁን ወደከተማይቱ ላኩ ከምግቦቿዋ የትኛው ንጹህ እንደሆነም ይመልከት ከርሱም ምግብን ያምጣላችሁ› ማለት ነው፡፡
የገበያዎች ሁኔታ ከትክለኛው የእስላምና ተግባራዊ ገፅታዎች አንዱ መሆኑ አያከራክርም፡፡ የስነ ምግባርን መልከም ገጽታ ለማየት ከፈለግን ወደ ገበያ ጎራ ማለት ጠቃሚ ነው፡፡ ሃይመኖትን እውነተኛ ወይም በገጽታ ብቻ የተወሰነ መሆኑን አስመልክቶ ፍርድ መስጠት የምንሻ ከሆነም ያን ሰው ሲሸጥና ሲገዛ ያለውን ሁኔታ ማጤን ይኖርብናል፡፡ ከዚህ ላይ (አላህ ይወድላቸውና) ከስይዲና ዑመር ፊት የቆመውን ሰውዬ ሁኔታ ልናስታውስ ይገባል፡፡

ሰይዲና ዑመር እንዲህ አሉት፡ ‹እኔ አንተን አላቅህም እኔ አንተን አለማወቄም አይጎዳህም፡፡ አንተ የምትከበረው በሚያውቅህ ሰው ነው፡፡ ያን ጊዜ አንድ ሰውዬ እኔ አውቀዋለሁ አለ፡፡ እሳቸወውም በምን በምን ታውቀዋለህ ሲሉ ተየቁት፡፡ በፍትህና በትረፋት በማለትም መለስ፡፡ አሳቸውም መግቢያ መውጫውንና የሌት ተቀን ሁኔታውን የምታወቀው ቅርብ ጎረቤትህ ነውን ሲሉ እንደገና ጠየቁት፡፡ አሱም አይ አይደልም በማለት መለሰ፡፡ እሳቸውም አንግዳውማ ጽድቅነት በሚለይባቸው በብርና ወርቅ የምተዋዋለው የንግድ አጋርህ ነዋ በማለት ጠየቁት፡፡ እሱም ኧረ እንደዚያም አይደልም በማለት መለሰ፡፡ ታዲያ መልካም ምግባር የሚለይበት የጉዞ ጓደኛህ ይሆን ሲሉ ጠየቁት፡፡ እሱም ኧረ አይደለም በማለት መለሰ፡፡ አሳቸውም አንገዳውስ አንተም አታውቀውም አሉና ወደሰውው ዞር በማለት አንተ የምትከበረው በሚያውቀህ ሰው ነው አሉት እንደገና፡፡
የመገበያየት ውል አንድ ሰው ትክክለኛ ሃይማኖተኛ ወይም በገጽታ አስመሳይ የሆነ ሰው ይለይበታል፡፡ ልቡ ከጸሎት እጅግ በጣም ሩቅ ሆኖ እያለ ሰዎችን ለማምታታትና ለማታለል በምላሱ ጸሎት የሚያዘወትር ስንትና ስንት ሰው አለ፡፡ በይዩልኝ ይስሙልኝ ገጽታ ተከልሎ ግንዘብ ለማግኘት የሚጠረው ሰው፣ ሰዎች ሃይማኖት የሚወዱ እንዲሁም ሃይማኖተኛን የሚያከብሩ መሆናቸውን ተመርኩዞ በተንኮል ገበያውን የሚያጧጡፈውም ሰው እጅግ ብዙ ነው፡፡

በሃይማኖት ለመነገድ አንዳንድ ሰዎች ከተጫበጩ ጋር የማይጣጣም ስያሜ ለበርካታ ነገሮች ሲጡ እናያለን፡፡ ይህውም በሃማኖት ስም ተከልሎ ገንዘብ ለማካበት በማሰብ ነው፡፡ ይህ ሰው በዚህ ዓይነት ተግባሩ ሃይማኖቱን እየጎዳና በሰዎች መንፈስ ዘንድም መጥፎ መንፈስ እየፈጠረ መሆኑን አያውቅም፡፡ አላህ (ሱ.ወ.ዐ.) እንዲህ ላል፡

وَمِنَ النَّاسِ مَنْ يُعْجِبُكَ قَوْلُهُ فِي الْحَيَاةِ الدُّنْيَا وَيُشْهِدُ اللَّهَ عَلَى مَا فِي قَلْبِهِ وَهُوَ أَلَدُّ الْخِصَامِ؛ وَإِذَا تَوَلَّى سَعَى فِي الْأَرْضِ لِيُفْسِدَ فِيهَا وَيُهْلِكَ الْحَرْثَ وَالنَّسْلَ وَاللَّهُ لَا يُحِبُّ الْفَسَادَ

ትርጉሙም ‹ከሰዎችም ውስጥ እርሱ ክርክረ ብርቱ ሲሆን በቅርቢቱ ሕይወት ንግግሩ የሚደንቅህና በልቡ ውስጥ ባለው ነገር ላይ አላህን የሚያስመሰክር ሰው አለ፡፡ (ካንተ) በዞረም ጊዜ በምድር ላይ በውስጧ ሊያበላሽና አዝመራንም እንሰሳትንም ሊያጠፋ ይሮጣል ፡፡ አላህም ማበላሸትን አይወድም፡፡› ማለት ነው፡፡

የእስልምና ሃይማኖት አንድ ሙስሊም ከሰዎች ጋር ገበያ በሚገበያይበት ወቅት የሚፈጽማቸው የገበያ ደንቦችና ስርኣቶች አስቀምጧል፡፡ ከነዚህ ደንቦች አንደኛውና ዋነኛው አላህን ማስታወስና ትእዛዙን መጠበቅ የሚለው ነው፡፡ አንድ ሙስሊም በማንኛውም ጊዜ ከቶ ሊለየው የማይገባ ነገር ቢኖር አላህን ማስታወስ የሚለው ጉዳ ነው፡፡ አላውን ማስታወስ ስንል በቃል ማወደስና የአካላት ተግባራትም ይካተታሉ፡፡ አንድ ሙስሊም ሴትም ይሁን ወንድ ወደገበያ ከመግባቱ በፊት የገባያ ጸሎትን ማድረስ ይኖርበታል፡፡

የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) አንድ ሰው ወደገበያ ሲገባ

**(لاإله لا الله وحده لا شريك له، له الملك وله الحمد، يحي ويميت، وهو حي لايموت، بيده الخير كلُّه وهو على كل شيئ قدير)**

የሚለውን ጸሎት ካደረሰ (ታላቁ አላህ እልፍ አላፍ መልካም ስራ ይምዘግብለታል አላፍ ኃጢያትም ያብስለታል በጀነትም ቤት ይሰራለታል፡፡) ብለዋል፡፡ እዚህ ላይ አላህን ማስታወስ ወይንም መዝከር ስንል በምላስ ብቻ አለመሆኑን ለማረጋጥ እንወዳለን፡፡ አላህን መዝከር የተፈቀዱ ነገሮችን በማጣራትና ከተከለከሉ ነገሮች በመራቅ መታነጽ ይኖርበታል፡፡

ሌላው የገበያ ደንብ ደግሞ **እውነተኛ መሆንና ከሃሰት መራቅ** የሚለው ነው፡፡ በመሰረቱ አንድ ሙስሊም በማንኛውም ወቅት እውነተኛ መሆን ይጠበቅበታል፡፡

አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ይላል፡

(ياأيها الذين أمنوا اتقوا الله وكونوا مع الصادقين)

ትርጉሙም ‹እናን ያመናችሁ ሰዎች ሆይ! አላህን ፍሩ ከጻድቃንም ጋር ሁኑ፡፡› ማለት ነው፡፡ ይህን ማለትም አንድ ሙስሊም በሚሸጥና በሚለውጥበት ጊዜ ገበያውን ለማሳካትና ለማጧጧፍ ሲል መዋሸት የለበትም ማለት ነው፡፡ የዚህ አይነቱ የገበያ ውሸት በዚህች አለም በረከትን ያስወግዳል በመጭው አለም ደግሞ ከታላቁ አላህ እዝነት ያርቃል፡፡ የሌላውን ሰው ገንዘብ በከንቱ ለመውሰድ በሀስት ለመማል እርኩስ መንፈሱ ገፋፍታው የማለ እንደሆነ ደግሞ ወንጀሉ እጥፍ ድርብ ይሆናል፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንዲህ ማለታቸው ተወርቷል፡፡ (ሺያጭና ገዥ እስካልተለያዩ ድርስ የማፍረስ ምርጫ አላቸው፡፡ እውነተኛና ግልጽ ከሆኑ በገበያቸው አላህ በረከትን ያሰፍናል፡፡ የዋሹና የደበቁ እንደሆነ ግን ከገበያቸው አላህ በረከትን ያነሳል፡፡) እንዲሁም ነብያችን እንደዚህ ብለዋል፡ (ሦስት ሰዎች ታላቁ አላህ የቂያማ እለት አያናግራቸውም አይመለከታቸውምም እንሱም አንት ካቀረብከው የበለጠ ዋጋ ተሰጥቸ ነበር በማለት በገበያ በሃሰት የማለ ሰው፣ የአንድን ሙስሊም ገንዘብ ቦጭቆ ለመወሰድ በሃስት የማለ ሰውና የተረፈውን ውሃ ሌላ ሰው እንዳይጠቀምበት የከለከለ ሰው ሚሉት ናቸው፡፡ ይህን ሰውዬ አላህ (ሱ.ዐ.) የቂያማ እለት እንዲህ ይለዋል (ዛሬ እኔ ትሩፋቴን እከለክልሃለሁ አንት በዚያች በጠፊዋ አለም አንት በእጅህ ያልሰራሃውን ውሃ እንደከለከልህ ሁሉ፡፡) ነብያችን አሁንም እንዲህ ይላሉ (የአንድን ሙስሊም ገንዘብ ቆርጦ ለመውሰድ ሀሰተኛ ሆኖ የማለ ሰው አላህን በሱ የተቆጣበት ሆኖ ይገናኛል) ነብያችን (ሰ..ዐ.ወ.) ባለደረቦቻቸውን አደራ በመሸጥ መለውት ወቅት ማሃላ እንዳታበዙ አሱ ንፍቅናን ያወርሳል እንዲሁም በረከት ያስወግዳልና በማለት ያስጠነቅቁ እንደነበር ተውርቷል፡፡

እንደሁም ከገበያ ደንቦች ሌላው **አመኔታ፣ እርካታና አለማታለል** የሚለው ጉዳይ ነው፡፡አመኔታ በገበያ ወቅት ሁለቱ ወገኖች ይረኩ ዘንድ ሙሉ ግልጸነትን ያካተተ መሆን አለበት፡፡ታላቁ አላህ እንዲህ ይላል፡

(إلا أن تكون تجارة عن تراض منكم)

ትርጉሙም ‹ግን ከናንተ በመዋደድ የሆነችን ንግድ(ብሉ)› ማለት ነው፡፡ ነብያችንም (ሶ.ዐ.ወ.) ለዑስማን ቢን አፋን(አላህ ይደድላቸውና) እንዲህ ብለዋል (በምትገዛበት ወቅት ይስፈሩለህ በምትሸጥበት ወቅት ደግሞ ራስህ ስፈር) አሳኢብ የተባሉት የነብያችን ባልደረባ ደግሞ እንዲህ ብለዋል  ከእለታት አንድ ቀን ወደነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ሄድኩኝ ሰዎችም ያመሰግኑኝና ያሞግሱኝ ጀመር ነብያችን ያን ጊዜ እኔ ከናንት የበለጠ አውቃለሁ አሉ፡፡ ስለሱ ማለታቸው ነበር እኔም አውነተዎን ነው እናትና አባቴን የማሳለፍለሁ የአላህ መልእክተኛ ሆይ የንግድ ሸሪኬ ነበሩ ምንም የማትደብቁና ማነንም የምትጠረጠሩ አጅግ መልካም ሸሪኬ ነበሩ አልኩኝ አሉ፡፡

ነበያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንዚያን አላህን የማይፈሩ የእርኩስ መንፈስ ባለቤት የሆኑትንና ሰዎችን ለማታለልና ገንዘባቸውን በከንቱ ለመውሰድ መጥፎ መንፈሳቸው የምተገፋፋቸውን ሰዎች ከማታለል እንዲርቁ (ያታለልን ሰው ከኛ አይመደብም) በማለት አጥብቀው አስጠንቅቃዋል፡፡

ነብያችን በሸርክ የሚሰሩ ሰዎች የአጋርነታቸው መሰረት ታማኝነትና እውነተኛነት እንዲሆን ምክር ለግሰዋል፡፡ እንዲህም ብለዋል (ታላቁ አላህ አንዱ ሌላውን አስካላታለለ ድረስ እኔ የሁለት ሸርክ ሰራተኞች ሦስተኛ ወገን ነኝ አንዱ ካታለለ ከመካከላቸው ገለል እላለሁ ብሏል)

ቀጣዩ የገበያ ደንብ ደግሞ **በሚዛን አለማታለል** የሚለው ጉዳይ ነው፡፡ ተጥፊፍ የሚለው የዐረበኛ ቃል ከሰውች ሲሰፍሩ ወይንም ዚመዝኑ አሟልቶ መስፈርና መመዘን ለሰዎች ሲሰፍሩ ወይንም ሲመዝኑ ደግሞ አጉድሎ መስፈር ወይም መመዘን ማለት ነው፡፡ ሌሎች መለኪያዎች ሁሉ እንደመስፈሪያና መመዘኛ ይወሰዳሉ፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) ሚዛንን በትክክል እንዲንመዝን አዞናል እንደዚህም ይላል፡

وَأَوْفُوا الْكَيْلَ إِذَا كِلْتُمْ وَزِنُوا بِالْقِسْطَاسِ الْمُسْتَقِيمِ ذَٰلِكَ خَيْرٌ وَأَحْسَنُ تَأْوِيلًا

ትርጉሙም ‹በሰፈራችሁም ጊዜ ስፍርን ሙሉ፡፡ በትክክለኛው ሚዛንም መዝኑ ይህ መልካም ነገር ነው መጨረሻውም ያማረ ነው፡፡› ማለት ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) የዚህ ዓይነት የሚዛን ማተለል የሚፈጽምን ሰው እንዲህ የሚል ዛቻ ሰንዝሮበታል፡፡

وَيْلٌ لِّلْمُطَفِّفِينَ الَّذِينَ إِذَا اكْتَالُوا عَلَى النَّاسِ يَسْتَوْفُونَ * وَإِذَا كَالُوهُمْ أَو وَّزَنُوهُمْ يُخْسِرُونَ

ትርጉሙም ‹ለሰላቢዎች ወዮላቸው! ለነዚያ ከሰዎች ባሰፈሩ ጊዜ የሚያስሞሉ፡፡
ለነሱም (ለሰዎች) በሰፈሩ ወይም በመዘኑላቸው ጊዜ የሚያጎድሉ (ለሆኑት)፡፡›
ነብዩ ሹአይብ (ዐ.ሰ.) ህዝቦቻቸውን የሰዎችን ገንዘብ አታሎ ከመውሰድና ከሚዛንና
ከመስፈር ከማታለል እንዲርቁ ማስጠንቀቃቸውን ቁርአን እንዲህ በማለት አውስቷል፡፡

وَإِلَىٰ مَدْيَنَ أَخَاهُمْ شُعَيْبًا قَالَ يَا قَوْمِ اعْبُدُوا اللَّهَ مَا لَكُم مِّنْ إِلَٰهٍ غَيْرُهُ قَدْ جَاءَتْكُم بَيِّنَةٌ

مِّن رَّبِّكُمْ فَأَوْفُوا الْكَيْلَ وَالْمِيزَانَ وَلَا تَبْخَسُوا النَّاسَ أَشْيَاءَهُمْ وَلَا تُفْسِدُوا فِي الْأَرْضِ

بَعْدَ إِصْلَاحِهَا ذَٰلِكُمْ خَيْرٌ لَّكُمْ إِن كُنتُم مُّؤْمِنِينَ

ትርጉሙም ‹ወደ መድያንም ውንደማቸውን ሸዓይብን (ላክን) እንዲህም አላቸው ወገኖቼ ሆይ! አላህን ተገዙ ከርሱ በቀር ምንም አምላክ የላችሁም ከጌታችሁ ዘንድ ግልጽ ማስረጃ በርግጥ መጥታላችኋለች፡፡ ስፍርንና ሚዛንን ሙሉ፡፡ ሰዎችንም አንዳቾቻቸውን (ገንዘባቸውን) አታጉድሉባቸው በምድርም ውስጥ ከተበጀ በኋላ አታበላሹ፡፡ ይሃችሁ ምእምናን እንደሆናችሁ ለናንተ የተሸለ ነው፡፡› ማለት ነው፡፡

ሌላው የገበያ ደንብ ደግሞ **የሌሎችን መብት አለመጋፋት** የሚለው ጉዳይ ነው፡፡ በመሆኑም ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) አንድ ሰው ወንድሙ የተስማማውን ነገር ለመግዛት እንዳይቀርብ አስጠንቀቀዋል፡፡ እንዲህም ብለዋል (ከፊላችሁ ወንድሙ ለጊዛ ያሰበውን ነገር አይግዛ) በሌላ ሓዲስ ደግሞ (ወንድሙ ሊገዛ ያሰበውን ነገር አይግዛ ካልፈቀደለት ወይም ትቶ እስካልሄደ ደረስ ወንድሙ አየተስማማ ያለውን ነገር ለመስማማት አይቅረብ) ብለዋል፡፡ አንድ ሰው ሌላው ሊጊዛ ካሰበው ነገር መራቁና የሱን እቃ ለመሸጥ ሲል የወንድሙን ሸቀጥ ከማራከስ መራቁ ከገበያ ተላላቅ ስርአቶች አንዱ እንደሆነ የእምነቱ ሊቆች አመልክተዋል፡፡

የሰዎችን ምግብ አደጋ የሚጥለውና በሀገር ላይ ከፍተኛ ወድቀት ሊያስከትል የሚችለው **ሸቀጥን በሞኖፖል ማካበት** የሰዎችን መብት እንደመጋፋት ይቆጠራል፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንዲህ ብለዋል (ስህተተኛ ሰው ካልሆነ በስተቀር ሸቀጥን በሞኖፖል የሚያካብት ሰው አይኖርም) ሸቀጥን በሞኖፖል የሚያካብት ሰው በዚህ መልኩ የሚያገኘው ትርፍ የእርም ገንዘብ መሆኑን የዘነጋና ራስ ወዳድነት አሸንፎት ለሰዎች ከማለት ይልቅ ለራሴ ማለትን የመረጠ ሰው ነው፡፡ ይህ እርም ገንዘብ በዚህች አለም እሱን አውዳሚ ከመሆኑም ባሻገር በመጭው አለምም ከአላህ እዝነት ለመራቁ ምክኒያት ይሆናል፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል (የሰዎችን የመምግብ ሸቀጥ በሞኖፖል ያካበተ ሰው አላህ (ሱ.ወ.) በጎንድሽ በሽታና በደድህነት ይቀጠዋል፡፡ እንዲሁም በሌላ ሐዲስ እንዲህ ብለዋል (የምግብ ሸቀጥን ለአርባ ቀን ያህል በሞኖፖል ያካበት ሰው እሱ ከአላህ ርቋል አላህም ከሱ ርቋል ማንኛውም በሰው ራህብ ለማድረስ ምክኒያት የሆነ ሰው የአላህ ጥበቃ ርቆታል)

እዚህ ላይ ገበያዎችን መቆጣጠር ከመንግስት አጠቃላይ ስልጣን አንደኛው መሆኑን ስናረጋግጥ የማታለል፣ የሞኖፖልና የብዝበዛን ወንጀሎች ለመከላከል ከሚመለከተው ወገን ጋር መተባበር መስራት የህዝቡ ግዴታ ነው እንላለን፡፡ ምክኒያቱም የዚህ ዓይነቱን አሉታዊ ገጽታ ማጥፋት የህብረተሰቡን የመንፈስ ደህንነት እውን በማደረግ ረገድና ለኢኮኖሚ ሂደቱ መፋጠን ታላቅ ሚና ስለሚኖረው ነው፡፡ በአንፃሩ ደግሞ ማታለልና ማጭበርበር ከብልሹነት በሮች ታለቁ ሲሆን የሀገሮችን ኢኮኖሚ በከፍተኛ ደረጃ ያወድማል፡፡

እንዲሁም ገበያዎችን መቆጣጠርና ማስተባበር ታለቅ ሃላፊነት ሲሆን ተጠያቂዎች የተጣለባቸውን ሃላፊነት ተወጥተዋል ወይስ አጓድለዋል የሚል ጥያቄ ከታላቁ አልህ በኩል ይቀርብባቸዋል፡፡

***ይህን ዓይ ነት ቃሌን ተናግሪያለሁ፡፡ ስለሱም ከአላህ ዘንድ ለኔና ለናንትም ምህረትን እጤቃለሁ፡፡***

ምስጋና ለአለማቱ ጌታ ለአላህ ይገባው፡፡ ከአለህ በስተቀር የሚገዙት አምላክ የለም ብቸኛ ሸሪክም የሌለው በመሆኑ እምሰክራለሁ፡፡ እንዲሁም ነብያችን ሙሐመድ የአላህ ባሪያና መልእክተኛው በመሆናቸውም እመሰክራለሁ፡፡ በርሳቸው በቤተሰቦቻቸው፣ በመላ ባልደረቦቻቸው የአላህ እዝነት ይውረድ፡፡

***ሙስሊም ወንድሞቸ ሆይ!***

*የሰዎች ምግብ፣ መጠጥና የሚያስፈልጓቸው ነገሮች ዋስትና ከሰብኣዊ ሙብት ቀደምትነት ያለቸው ማህበራዊና ሰብኣዊ ጉዳዮች ናቸው፡፡ አንድ ሰው የምግቡና የመድሃኒቱ ደህንነት ሳይከበርለት ከበሬታ ያለው ኑሮ ያገኛል ማለት ዘበት ነው፡፡ በመሆኑም የማጭበርበርና የሸቀጥ በተለይም ደግሞ የምግብና የመድሃኒትን ሞኖፖል አደጋን ለመቋቋም የተቀናጀ ጥረት ማድረግ ያስፈልጋል፡፡*
*ይሁንጂ ሃይመኖቱን ጠንቅቆ የሚያቅ ነጋዴ የአላህ ኢባዳ በማደረስ፣ በመስግድና መፆም እንዲሁም እንደምጽዋትና አመኔታ በአሉ መልካም ምግባሮቹ ይታወቃል፡፡ በርካታ ፆመኞች ከረሃብና ከውሃ ጥም የዘለል ትርፍ የላቸውም፡፡ አያሌ የሌለት ሰጋጆችም ከድካምና እንቅልፍ ከማጣት ያለፈ ጥቅም አያገኙም፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እውነተኛና ታማኝ የሆነ ነጋዴ ደረጃ ከፍተኛ መሆኑን ገልጸዋል፡፡ እንዲህም ብለዋል፡፡ (እውነተኛና ታማኝ የሆነ ነጋዴ ከነብዮች፣ ከጻዲቃንና ከሰምአታት ጋር ይሆናል፡፡) እንደዘሁም እንዲህ በለዋል፡ ( እጅግ ጥሩ የሆነው ስራ የነዚያ በተናገሩ ጊዜ የማይዋሹት፣ አደራ በተሰጣቸውም ወቅት አደራን የማይበሉት፣ ቃልም በገቡ ጊዜ ቃላቸውን የሚያከብሩት፣ በሚገዙም ጊዜ የማያንቋሽሹት፣ በሸጡም ጊዜ ከልክ በላይ ያማያወድሱት፣ በተበደሩም ጊዜ ነገ ዛሬ ያማይሉት፣ በአበደሩም ጊዜ ውጥር አድርገው የማይዙት ነጋዴዎች ስራ ነው፡፡) ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) በሌላ ሐዲስ እውነተኛ ነጋዴ የሱ ጥላንጂ ሌላ ጥላ በሌለበት በቂያማ እለት በአላህ ጥላ ስር እንደሚሆን እንዲህ በማለት አብስረዋል (እውነተኛ ነጋዴ በቂያማ እለት በዐርሽ ጥላ ስር ይሆናል፡፡)*
*ሁላችንም የውጤቱ ተጠቃሚ የምንሆንበት አጠቀላይ እርቀ ሰላም እንዲሰፍን ቢጋራ መስራት እጅጉን ያስፈልገናል፡፡ እያንዳንዳችን ወንድሞቻችንን በእዝነት ዓይን ማየትና ለራሳችን የምነወደውን ነገር ሁሉ ለነርሱም ልንወድላቸው ይገባል፡፡ ይህን ዓይነት መልካም ምግባር እውን ለማድረግ ደግሞ ሻጭ ለገዜ ልክ አሱ አንዲመገዛ ሆኖ ታማኝ እንዲሁም ገዢው ልክ እሱ እንደሚገዛ ሆኖ ታማን መሆንን ግድ ይላል፡፡ ይህም ገጽታ የእምነት መገለጫ ነው፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንዲህ ብለዋል፡፡ (አንዳችሁ ለራሱ የሚወደውን ለወንድሙም እስካልወደደ ድረስ ሙእሚን አይሆንም፡፡)*

**اللهم أغننا بحلالك عن حرامك واكفنا بفضلك عن من سواك**